# የልዩ አመጋገብ ፍላጎት ቅጽ

## የትምህርት ዓመት 2024-2025

Division of Food & Nutrition Services
የምግብ እና ንጥረ-ምግብ አገልግሎት ክፍል
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Gaithersburg, Maryland 20879

## ሰክሽን A—በወላጅ/አሳዳጊ መሞላት አለበት።

የተማሪ ስም ______________________ የተማሪ መታወቂያ ቁጥር__________ የክፍል ደረጃ____

የትምህርት ቤት ስም ______________________ የትምህርት ቤት ቁጥር__________

የአስተማሪ ስም ______________________

የወላጅ/የአሳዳጊ ስም (ይጻፉ) ______________________

የወላጅ/አሳዳጊ ፊርማ ______________________

ኢ-ሜይል______________________

የስልክ ቁጥር_____-_____-______ ቀን____/____/_____

## ሰክሽን B—በሀኪም መሞላት አለበት።

ተማሪው(ዋ) የማይስማማው(ት) ምግብ አለ? ❑ አዎን ❑ የለም

አዎን ከሆነ፥ እባክዎን ከዚህ በታች ካለው ዝርዝር ውስጥ የማይስማማው(ት)ን አይነት ምግብ ይግለጹ

- ❑ ስንዴ/Wheat
- ❑ ወተት/Dairy
  - ❑ ወተት ያለበት የበሰለ ምግብ ይቻላል/ Milk baked in products are ok (ማለትም ፓንኬክ)
  - ❑ እርጎ ይስማማል/Yogurt is OK
  - ❑ ቺዝ ይስማማል/Cheese is OK
- ❑ ለውዝ/Tree Nuts
- ❑ እንቁላል/Eggs
  - ❑ የበሰለ እንቁላል ያለበት ምግብ ይቻላል/ Eggs baked in products are ok (ማለትም ፓንኬክ)
- ❑ አኩሪ አተር ይስማማል/Soy
- ❑ አኩሪ አተር ይስማማል/Soybean Oil is OK
- ❑ ኦቾሎኒ/Peanuts
- ❑ ዓሣ/Fish
- ❑ ሼል ፊሽ/Shellfish
- ❑ ሰሊጥ/Sesame

ሌላ፡- ______________________ ሌላ፡- ______________________

ተማሪው(ዋ) ሌላ ልዩ የአመጋገብ ወይም የምግብ ፍላጎቶች አሉ(ሏ)ት? ❑ አዎን ❑ አይደለም

እባክዎን የተለየ የምግብ ዝግጅት (ማለትም ጭማቂ)፣ የድድ በሽታ፣ የስኳር በሽታ፣ ወዘተ የመሣሰሉ ልዩ የምግብ ፍላጎቶችን ይግለጹ።

______________________

______________________

______________________

ከላይ የተጠቀሰ(ች)ው ተማሪ ልዩ የትምህርት ቤት ምግብ እንደሚያስፈልገው/እንደሚያስፈልጋት አረጋግጣለሁ።

የሐኪሙ ስም (ይጻፉ) ______________________ የቢሮ ስልክ ቁጥር_____-_____-______

የሐኪም ፊርማ ______________________ ቀን ____/____/_____

ይህ ተቋም በእኩልነት የሚያገለግል ድርጅት ነው።

# የልዩ ምግብ ፍላጎት መግለጫ

Division of Food & Nutrition Services
የምግብ እና ንጥረ-ምግብ አገልግሎት ክፍል
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ
Gaithersburg, Maryland 20879

## የበፊት ታሪክ መረጃ፡-

የአካል ጉዳተኝነት ያለባቸው አሜሪካኖች ህግ (ADA) ላይ አብዛኞቹ የአካል እና የአዕምሮ እክሎች የአካል ጉዳተኝነት መሆኑ ተገልጿል። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የምግብ እና ንጥረ- ምግብ አገልግሎት ክፍል/MCPS Division of Food and Nutrition Services (DFNS) በትምህርት ቤት የምግብ ፕሮግራም ላይ የመሳተፍ እና የፕሮግራሙን ጥቅማ ጥቅሞች ለማግኘት እኩል የተጠቃሚነትን እድል መኖሩን ለማረጋገጥ ከወላጆች እና ከሌሎች የዲስትሪክት ሰራተኞች ጋር በትብብር ይሰራል። ትምህርት ቤቶች የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ምግብ በሚስማማቸው አይነት ማስተካከል አለባቸው። ይህ ምግብን የማስተካከል ሁኔታ የሚከናወነው በተማሪዎቹ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ የሚቀርቡት ጥያቄዎች ፈቃድ ካለው የጤና ባለሙያ በጽሁፍ መግለጫ ሲደገፍ ብቻ ነው— የልዩ ምግብ ፍላጎት መግለጫ ቅጽ (ገጽ 1) )። ትምህርት ቤቶች የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች አመጋገባቸውን በቀጥታ ለሚነኩ ሁኔታዎች የምግብ ማስተካከያ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። አጠቃላይ የጤና ስጋቶች፣ ለምሳሌ ወላጅ ለተማሪው(ዋ) የተሻለ ነው ብሎ ስለሚያምን አንድ ተማሪ ከግሉተን-ነጻ ምግብን እንዲመገብ የሚፈልጉ ከሆነ፣ የአካል ጉዳተኝነት ስላልሆነ ልዩ የምግብ ዝግጅት አይደረግላቸውም። DFNS በአመጋገብ ፕሮግራም አዘገጃጀት መደበኛ የአካል ጉዳቶችን ለማስተናገድ የምግብ እቅድ ይነድፋል። አብዛኛውን የአካል ጉዳተኞች በመደበኛው የስርዓት ምግብ ዝግጅት መስተናገድ ይችላሉ። DFNS የተጠየቀውን የተለየ የምግብ ለውጥ ወይም ሌላ ማሻሻያ እንዲያቀርብ አይጠበቅበትም፥ ነገር ግን ምክንያታዊ የሆነ የምግብ ለውጥ የተማሪን የአካል ጉዳት የሚረዳ እና በፕሮግራሙ ውስጥ የመሳተፍ ወይም የመጠቀም እኩል እድል ይሰጣል።

## የአፈጻፀም ሒደት

አንድ ጊዜ የተለየ የምግብ ፍላጎት ቅጽ ከተሞላ በኋላ፣ ቅጹ እንዲደርሳቸው [DFNSOffice@mcpsmd.org](mailto:DFNSOffice@mcpsmd.org) DFNS central office የጽሕፈት ሠራተኛ በኢሜይል ይላካል። የሐኪም ፊርማ ጭምር የተለየ የምግብ ፍላጎት መግለጫ ቅጽ ከተሞላ በኋላ፣ ቅጹ ፈቃድ ላላቸው የአመጋገብ ባለሙያዎች ይተላለፋል፥ ከዚያም ለተማሪው(ዋ) የምግብ ዝግጅት እቅድ ለማዘጋጀት ከወላጅ(ጆች)/አሳዳጊ(ዎች) ጋር ይገናኛሉ። ፈቃድ ያለው/ያላት የአመጋገብ ባለሙያ እና ወላጅ(ጆች)/አሳዳጊ(ዎች) በአመጋገብ ፕላን ከተስማሙ በኋላ ሰራተኞቹን ማሰልጠን እንዲጀምር እና አስፈላጊ ከሆነም ምግብ ማዘዙን ለመርዳት እቅዱ ወደ ት/ቤቱ ሱፐርቫይዘር ይላካል። የምግብ ዝርዝሩ መለጠፍ ያለበት በትምህርት ቤቱ ካፌቴሪያ ውስጥ በተገቢ ቦታ ላይ ሲሆን የካፌቴሪያው አስተዳዳሪ እና ሰራተኞች የሚደርሱበት ቦታ መሆን አለበት። አንዳንድ ተማሪዎች የተዘጋጀላቸው ምግብ እንዳይበከል ታሽጎ እንዲቀመጥላቸው ሊፈልጉ ይችላሉ። እባክዎ ያስተውሉ፡ ልዩ የምግብ ፍላጎት መግለጫ ቅጽበተናጥል ወይም ከ504 ፕላን በተጨማሪ መተግበር አለበት።